# የኢትዮጵያ የፖለቲካና የሲቪክ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የጋራ መርሆና የትግል ጥሪ

በሥልጣን ላይ ያለው የሕወሐት/ኢሕአዴግ አገዛዝ፤ ከዚህ በፊት ሌሎች አምባገነኖች የገጠማቸውን ዕጣ ፈንታ ለመቀበል የተቃረበበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የአምባገነኑ አቶ መለስ ዜናዊ በጠና መታመምን ተከትሎ ሊፈጠር የሚችለውን የስልጣን ክፍተትና ሽኩቻ እንዲሁም እየተካሄደ ያለው የሕዝብ መነሳሳት የሚያስከትለው ሁኔታና ወዴት እንደሚያመራ በቅጡ ለመተንበይ ያዳግታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፤ የአገዛዙን ውድቀት ለማቀላጠፍ፤ የግለሰብና የቡድን/የወል መብቶች የተከበሩባት፤ ፍትሐዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለማቋቋም በሚደረገው ወሳኝና የመጨረሻ ትግል፤ ለፍትህና ለእኩልነት የሚታገሉ ኃይሎች በሙሉ፤ ከወዲሁ ተዘጋጅተውና ተባብረው ትግሉን መምራት እንደሚገባቸው እናምናለን፡፡

ከየአቅጣጫው የሚመጡት መረጃዎችና በኢትዮጵያ የሚታዩት ክስተቶች የሚጠቁሙት፤ ሕውሐት/ኢሕአዴግ አገሪቱን ለማስተዳደር እየተሳነው መምጣቱን ስለሆነ፤ በጋራ ታግለን ሕዝባችንን ለሚመኘው ድል የምናበቃበት ጊዜ አሁን ነው።
ስለዚህም፤ በዚህ መግለጫ የተካተትን ተቃዋሚ ኃይሎች ጥንቃቄ በተሞላው ዘዴ፤ የአገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታዎች በመከታተል፤ ኃይላችንን በማስተባበር ትግላችንን በማቀናጀትና በማጠናከር ከዚህ በታች በተዘረሩት መርሆዎች ዙሪያ በጋራ ለመስራት ተስማምተናል።

ይህን አብይ ዓላማ ከግብ ለመድረስ ይረዳን ዘንድ፡ በኢትዮጵያ ፍትህ፤ ዴሞክራሲ፡ እኩልነትና ነጻነት እንዲሰፍን የምንታገል ኃይሎች (የፖለቲካም የሲቪክም ድርጅቶች)፤ የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች የትብብራችን መሰረት አድርገናቸዋል፤

1. የትግሉና የትብብሩ ዓላማ በኢትዮጵያ አንድነት ስር አስተማማኝና በህዝብ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሰረት ዘላቂ ዲሞክራስያዊ ሥርዓትን ለመመስረት ይሆናል፤

2. የዲምክራሲያዊ ሥርዓቱን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለመገንባት፤ ሁሉንም የዲምክራሲ ኃይሎች የሚያሳትፍ የሽግግር ሂደት እንዲኖርና፤ በህዝቡ ሙሉ ተሰትፎ በሚረቀቅ ህገ መንግስት ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት እንዲሰፍን እንታገላለን።

   ሀ. ይህንንም ሂደት የሚከታተል፣ የመረጃ ልውውጥና የድርጅቶቹን ግኑኝነት የሚያቀላጥፍ፤ አገር ውስጥና በውጭ

አገር ካሉት ከሁሉም ተሳታፊ ድርጅቶች የተወጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ እናቋቁማለን።

ለ. አስተባባሪ ኮሚቴው በየወቅቱ የሚታዩትን ሁኔታዎች እየገመገመ፤ ሁሉም በተስማሙበት በጋራ መወሰድ ያለባቸውን አቋሞችና ዕቅዶችን ያወጣል ።

3. የዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታውን የሚያኮላሽ፣ የሃገሪቱን ሉዓላዊነት የሚፈታተንና ማንኛውም ጣልቃ ገብነት እንቃወማለን፣ በጽናትም እንታገላለን።

4. ዲምክራሲያዊ ስርዓትን ከመመስረት ውጭ፤ ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን በማግለል፡ በሌላ አቋራጭ በተናጠል የሚደረግ ማናቸውንም ድርድር አጥብቀን እንቃወማለን። እንታገላለንም።

5. ሁሉም ዜጎች በዘር፣ በብሄር ብሄረሰብ በሃይማኖት ሳይለያይ ከላይ በተጠቀሱት መርሆች ዙሪያ በያሉበት በኢትዮጵያዊነት እንዲሰባሰቡ፤ በትብብር፤ በመቻቻልና በጋራ እንዲታገሉም ጥሪ እናቀርባለን።

በዚህም መሠረት፤ በኢትዮጵያ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ሥርዓት እንዲኖርና አገራችን ከምትገኝበት ቀውስና ውድቀት ወጥታ፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሰበዓዊ መብቶችና የብሄር/ብሄረሰቦች እኩልነት የሚጠበቅበት፤ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመፍጠር ሁሉም ዜጎች በጋራ እንዲታገሉ አገራዊ ጥሪ እያቀረብን፤ በተለይም፣

1. የጦር-ሠራዊቱ ሃላፊነት አንድን ድርጅት ወይም አንድን ግለሰብ ለማገልገል ሳይሆን የአገሪቱን አንድነትና ሉዓላዊነት የህዝብን ደኅንነት ለመጠበቅ መሆኑን ተገንዝቦ፤ በዚህ ፈታኝ ወቅት ከህዝቡ ጎን እንዲሰለፍ ጥሪ እናቀርባለን።

2. በሕወሐት/ኢህአዴግ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ለውጥ-ፈላጊ ሀይሎች/ግለሰቦች፤ ለዲሞክራሲ ከሚታገሉ ኀይሎች ጋር እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርባለን።

3. አገዛዙ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ፤ የእምነት ተቋማትንም እንዳያረክስ፤ ኢትዮጵያዊያን የሚያደርጉትን ትግል እየደገፍን፤ ከሁሉም የዲምክራሲ ታጋዮች ጋር በመተባበር ለአጠቃላይ ዲምክራሲያዊ ለውጥና ለዜጎች መብት መከበር እንዲታገሉ፤ በሃይማኖት ምክንያት አንዱ ከሌላው እምነት ተከታዮች ጋር እንዲጋጩ የሚደረገውን የመንግስት ሴራ በንቃት እንዲከታተሉና እንዲያከሽፉ እንጠይቃለን።

4. የኢትዮጵያ ህዝብ የሕወሀት/ኢህአዴግ አገዛዝ በዘርና በሃይማኖት ከፋፍሎ ለመምታትና ለመግዛት የሚያደርገውን ተንኮል ተገንዝቦ ተንኮሉን

እንዲያከሽፍና፤ ትግሉን አስተባብሮ ያለውን ሥርዓት በእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት በጋራ እንዲታገል ጥሪ እናቀርባለን።

5. ሁሉም የኅብረተስብ ክፍሎች፤ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ምሁራን፣ ተማሪዎች፤ በጋራ በመሆን ለሃቀኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ለፍትሕ፥ ለነፃነትና ለእኩልነት በህብረት እንድንታገል ብሔራዊ ጥሪ እናቀርባለን።

እነዚህን መሰረታዊ ዓላማዎች አንግበን የምናደርገው ትግል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትሕ፤ ነጻነት፤ እኩልነትና በሕዝብ ፈቃድ ላይ የተመሰረት ህገመንግስታዊ ስርዓት እስከሚቋቋም ድረስ እንደማይቋረጥ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል እንገባለን።

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
2. ጥምረት ለነፃነት ለእኩልነት ለፍትህ በኢትዮጵያ
3. የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሂደት
4. ብሩህ ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ንቅናቄ
5. የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (በጀ/ል ከማል ገልቹ የሚመራው)
6. የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት
7. ዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ንቅናቄ ለለውጥ በኢትዮጵያ/በቃ
8. መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መ.ኢ.ሶ.ን)
9. የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
10. Advocacy for Ethiopia
11. March 4 Freedom

ዕለት ነሓሴ 1, 2004 ዓም